In light of the above three points, one may only conclude that neither the source of the law nor the influence of local customs or customary laws were the reasons for the exceptional stand. Moreover, the fact that Article 44 of the draft was unchanged during the deliberations of the Codification Commission shows that this was originally inserted by the drafter and passed without objection. It should also be noted that despite the fact that many articles under Title XI of the Civil Code are verbatim copies of the copyright law of France, the drafter did not give anywhere his reasons for making such an exception on translation rights. Thus, in the absence of background materials, indicative of the reason(s) behind this exception, one may only guess the rationale behind it.[55]

---

[50] Supra, note 39.
[51] Finkelstein, H, Supra Note 27, at p. 53, footnote No. 6.
[52] Supra Note 38.
[53] The Article reads in French as follows:
Traductions
(1) - L'auteur ne peut s' opposer a la traduction de son oeuvre.
(2) - La traduction faite sans l'autorasation de l'auteur doit mentionner de facon express, au debut de l'ovrage cette circonstance.
(3) - Faute de cette mention, elle est reputee porter atteint aux droit de l'auteur."
[54] See, *Civil Codification Materials*, Book 3, Property (Unpublished, Law Library Archives), pp. 12 - 20 and p. 177 for amendments on Title XI (Minutes of January 8, 1958).
[55] See Major Issues on Translation Rights, Infra, 5

### 4.3 Translators' Rights.

Under the Civil Code of Ethiopia, translations are protected as original works, without prejudice to the rights of the author of the original work.[56] Accordingly, translators are assimilated to authors and as far as their (translated) works are concerned, they have equal rights with authors. Translators, however, cannot object to the retranslation of their works, for the same right is not given to authors.[57] Thus, as far as translators' rights are concerned, the copyright law of Ethiopia is consistent with major international copyright convetions as well as the domestic legislation of many courntries.

## 5. Major Issues on Translation Rights.

It is noted above that the Ethiopian copyright law took a unique stand on translation rights in contrast with major international conventions and domestic laws of many other nations. Moreover, despite the fact that the law was imported from France, it was noted above that the law deviated from its source and that no explanation was given for this either by the drafter or the Codification Commission. In light of these facts, it will be important to inquire into the reason(s) that compelled the law maker to enact such a law and also show the difficulties to be encountered in implementing the law. Accordingly, the following discussion will address issues such as: What was the motive of the drafter or the legislature in depriving authors of their right to deny authorisation for the translation of their works? If there were any convincing reasons for this during the making of the law, i.e., in 1960, are these reasons still valid today three and a half decades after the enactment of the law? To what extent have Ethiopian translators availed themselves of this right? and finally, though authors do not have the right to authorise the translation of their works, can they demand the payment of royalties from translators?

In the absence of an authoritative document showing the legislative intent behind Article 1655, it is admitted that the quest for the rationale cannot be anything but a guess. Accordingly, the first reason that may come to one's mind is the need to draw from the advanced literary cultures of other nations, in particular for educational purposes. This, as noted above, is the stand of many developing countries during negotiations on international conventions. Though this appears to be logical, since Ethiopia is not a party to any one of the international conventions to date, she is not obligated to protect foreign literary works. Thus, the Civil Code provisions are applicable to indigenous literary works only, but not to foreign works. It should, however, be noted that in 1958, i.e., during the making of the copyright law, the Codification Commission was not totally unaware of the need to acquire literary works for educational purposes, for it was then decided by the Commission to amend Article 49 of the draft (the current Article 1660 of the Civ. C.) so as to include the following sub-article:

> ***(3) - Where the work is out of print, copies or reproductions thereof are authorised in several copies if made for educational purposes.***[58]

---

[56] Article 1649. C.C

[57] Article 1655(1). C.C.

[58] See *Civil Codification Materials*, supra note 53 (C.C. 79). The Frech text reads as follows: Les Copies ou reproductions sont authorisees plusieurs exemplaires, a des fins d'ensignement, lorsque l'ouvre est epuise.

But, again for an unknown reason, neither the Amharic (which is the controlling version) nor the English version of the Code contains this sub-article. Moreover, public authorities are given the power to authorise the presentation, reproduction, or adaptation of literary works in the "general interest", which may arguably include educational purposes.[59] It should, however, be noted that though the advancement of education at the cost of authors' rights was the concern of the legislature, neither of the above cited Articles, 1660 or 1673, deals with translation rights, for translation is made free to all under Article 1655. It, therefore, appears that the reason for restricting translation rights was not for educational purposes, for had it been this, the legislature would have included the exception under either of the above cited articles.

In the absence of a clear legislative intent or rationale, one may also guess that the legislature intended to enrich the literary culture of the nation by allowing translators to translate any work without the necessity of seeking authorisation or formal licensing to make their works available to the general public. It may also be added that this may help to strengthen the cultural integration between peoples of different cultures and languages living in the nation. Though this seems to be a noble idea, whether Ethiopian translators have availed themselves of this freedom is a matter of opinion. It is, however, apparent that Ethiopian translators, for one reason or another, are not yet interested in translating local literary works into other local languages and this is a fact that can be seen from the display of books in every book shop. Despite the fact that the first printing press was introduced in 1897 and the nation has abundant protected literary works,[60] a significant number of translated works, most of them from English to Amharic started to be produced in the early 1980s. Nonetheless, the quality of translated works has been questioned by critics at different times.[61]

Though it is clear from the above that there is an apparent scarcity of literary works translated from one local language into another, there seems to be a good opportunity in the future to produce such works for many other languages are currently used as mediums of instruction and official languages in their respective regions. Moreover, many literary works as well as official gazettes and journals, have started to be published recently in different local languages. However, despite the free hand given to translators under Article 1655 of the Civil Code, whether Ethiopian translators will use the freedom to translate original literary works from one local language into another or continue translating only foreign works remains to be seen.

A related issue with regard to translation rights is whether or not authors of original literary works are entitled to remuneration (royalties) when their works are translated. It is shown above that under the Civil Code, an author cannot object to the translation of his work. Moreover a translator who translates a literary work without the authorisation of the author is mandatorily required to expressly state this fact at the beginning of the work and failing such a statement, it shall be deemed to be prejudicial to the author's right (Article 1655). This is the only provision that deals with the legal relation between an author and a translator.

---

[59] Article 1673. (C.C.)

[60] Note. Between 1940 and 1949(1948 and 1957 G.C.) 100 books, most of them Amharic original works, were published per year. See - Asfaw Damte, *Ye Amarigna Tebebe Kalat* (1940 - 49 E.C.), *Tobia* Monthly Bulletin 1st Year, No. 9. (1985 E.C.) p. 40.

[61] Melekete Tesfa, *Ye Tirgum Serawoch Ateyayakinet* (The Questionability of Translated works), *Mahlet* Monthly Bulletin, Vol. I, No. 1, (1985 E.C.), pp. 20-33.

Apart from the above, Title XI of the Civil Code does not provide a clear answer as to whether an author is entitled to claim a royalty from a translator. Moreover, remuneration even in cases of reproduction (publication) is not treated under the Title, but under Title XVI (contracts for the performance of services) and in particular under chapter 7, which deals with "publishing contracts". It should be noted that Article 1664 of the Civil Code (under Title XI) makes a reference to this chapter.[62] Accordingly, Articles 2692 through 2694 deal with "authors' remuneration" However, the conditions of remuneration under these articles are limited to the contract to be entered into between the author and the publisher as defined under Article 2672 and not applicable to the relationship between authors and translators.[63]

In light of the above, and in particular in the absence of a clear legal provision which allows or disallows the payment of royalties to authors in cases when their works are translated, one may easily note that the issue is open to interpretation. The fact that there are no any authoritative texts written on the subject[64] also contributes to the problem at hand. One may, however, argue that since the law has not expressly disallowed the payment of royalties, authors may claim remuneration from translators in cases where their works are translated. This may also be substantiated by the fact that had the legislative intent been to disallow this right, it would have provided a clear provision to this effect and, therefore, what is not disallowed under the law is allowed. Moreover, in a case where a translator wishes to translate a given literary work with the authorisation of the author,[65] the latter can have the opportunity to enter into a contract with the former and agree on the sum, or withdraw his consent, in which case the translator will be forced to translate without authorisation and state this fact in the translated work.

---

[62] Article 1664 - Makes reference to rules governing contracts of publication.
The conditions on which literary or artistic rights of ownership may be assigned by the author to third parties shall be as provided for by the chapter of the code relating to "contracts of publication" (Articles 2672-2697).

[63] Chapter 7. Publishing Contracts.
A publishing contract is a contract whereby a party, hereinafter called the author, assigns in whole or in part his incorporeal right in a literary or artistic work to the other party, hereinafter called the publisher who undertakes to reproduce or produce the work and distribute it to the public. Note that Art. 2680 imposes on publishers the duty to seek the authorisation of authors in case when they want to translate literary works submitted for publication. The article reads as follows: Article 2680 - Modification and Translation. An authorisation to reproduce or produce a work shall not imply an authorisation to adapt it, to modify it or to authorise its translation. Under Title XI of the civil Code, an author has the right to authorise the adaptation (Article 1654) and prevent the alteration of his work (Articles 1665 and 1671), but not the right to authorise the translation of his work. (Artilce 1655).

[64] The only works done in this area are the following three senior papers written by graduating students at different times:
1. Shifa Soressa, supra note 38.
2. Tamru Wendimagegnehu, *Some Aspects of the Ethiopian Law of Literary and Artistic Property-an Inquiry into the Source and Scope of Protected Rights*, (Unpublished, Law Library archives), (1971).
3. Seleshi Zeyohannes, *The Ethiopian Law of Literary and Artistic Property*, (Unpublished, Law Library archives), (1983). Note also that while Tamru argues that "...the pecuniary benefits from ...translated works accrue to the translator..."(p.53), Shifa on the other hand maintains that "(W)hat Article 1655 purports is the possibility of translating a work without securing authorisation from the author. But, in no way does it deprive the author of material remuneration. ...Thus, the phrase "without prejudice to the rights of the author of the original work" in Article 1649 should be interpreted in such a way to protect both economic and moral rights of the original author." (pp. 35 and 36).

[65] Note that this is not forbidden by law. See Article 1655 (C.C.).

On the other hand, one may also argue that the law, by stripping authors of their right to deny authorisation for the translation of their works, has at the same time stripped them of the right to remuneration by translators. This is so for the reason that Article 1655 purports to protect the "right of paternity" only, for it is expressly provided that "failure to state the fact that a translation is made without the authorisation of the author, shall be deemed to be prejudicial to the author's right" and nothing more. Thus, the non-payment of royalty by a translator is not prejudicial to the author's right. Moreover, when one looks at Article 1655 from a practical point of view, if translators are not legally required to seek the authorisation of authors - unlike in cases of publication, production, reproduction, and adaptation[66] there cannot exist a contract between the two parties (i.e. the author and the translator) and, therefore, no agreement on the sum to be paid.

As far as moral rights of authors are concerned, the law expressly provides under Article 1665 that "notwithstanding any stipulation to the contrary, the author may prevent his work, if altered by a third party, from being presented as the author's own". Moreover, authors may also seek civil and penal remedies in cases where their moral rights are affected.[67] This may arguably extend to authors' right over translated works and it appears that they can demand the correct translation of their original works without any alteration.

---

[66] See Articles 1652 - 1654 of the C.C.

[67] See Articles 1674 of the C.C. and Articles 675-679 of the Penal Code of Ethiopia. The Penal Code seems to limit the scope of protection to the right to authorise the production and reproduction of protected works.

## CONCLUSION AND RECOMMENDATIONS

Creators of works of the mind have enriched the cultures of their societies and the world at large through their efforts to create new ideas and express them in different forms. The present level of cultural development would not have, therefore, been achieved without the endeavour of creators of works of the mind who have toiled and even sacrificed many other interests to create new works. Authors, as creators of works of the mind, have also contributed to the development of the literary cultures of their fellow citizens.

Due to the fact that authors have the incorporeal right of ownership only over their works and that the corporeal right of ownership is exercised by others, literary works are vulnerable to a variety of unauthorised uses. Accordingly, literary works can be published, produced, adapted, and translated without authorisation or remuneration. Piracy of such works is, therefore, prevalent in many countries, in particular those that have weak copyright laws and inefficient enforcement mechanisms. In order to curb such practices, international conventions, as well as domestic copyright laws of many nations, give due recognition to and protect the moral and economic rights of authors.

Ethiopian copyright law, however, for an unknown reason deprives authors of their right to deny the authorisation for the translation of their works. Moreover, the law does not expressly provide that authors are entitled to remuneration from translators in cases when their works are translated without authorisation. The issue is, therefore, left open for interpretation.[68] The following suggestions are, therefore, made in order to fill the lacunae created by the law and make Ethiopian copyright law consistent with international conventions, to which Ethiopia may possibly make herself a party in the near future.

1. Major international conventions, which were originally tuned to the interests of the developed countries have only recently started to respond to the interests of the developing countries, too. Accordingly, the periods of protection, in particular for those works to be employed for the purposes of teaching, scholarship, and research, have been drastically reduced so as to accommodate the interests of developing nations. Many developing nations, including African nations are, therefore, parties to the international conventions discussed above.[69] Since all other provisions of the copyright law of Ethiopia are more or less consistent with these conventions, Ethiopia should amend Article 1655 of the Civil Code and make herself a party to the Universal Convention, which has a wider scope application and a comparatively larger number of member countries than the Berne Convention.

2. So far, the absence of translated works from one local language into another might not have necessitated the need to revise the law. The current usage of different languages for official and academic purposes, however, will soon create favourable conditions for the translation of original local literary works into other local languages. Thus, the amendment of the law will be timely and beneficial to local authors who are stripped of their rights for unknown reasons.

---

[68] There are no reported cases on this particular issue.

[69] For list of countries that joined the two Conventions, see Boguslavisky, M. supra note 32 pp. 93 and 95.

3. The law should also expressly provide that authors are entitled to remuneration from translators, for the latter's creative works are derivative and not original.

4. It is, therefore, suggested that the following Articles should be amended to read as follows:

Article 1655 - Translations

Only the author shall have during his life the right to authorise the translation of his work.[70]

Article 1670 - Heirs of the author - 1. Pecuniary rights.

(1) The author's right to authorise the production, reproduction, adaptation or translation of his work may, after his death, be exercised by his heirs for a period of fifty years from the time of publication of the work.[71]

Article 1673 - Rights of Public authorities.

(1) Public authorities may in the general interest, notwithstanding the author's opposition, authorise the presentation or reproduction or its translation or adaptation, after such work has been published by its author or his heirs.[72]

[70] With this amendment, Sub-Articles 2 and 3 of Article 1655 will be redundant and should, therefore, be deleted.
[71] Sub-Article 2 should be maintained as it is.
[72] Sub-Articles 2 and 3 should be maintained as they are.

እንደመሆናቸው መጠን ሕግ የደራሲያን ዝና፣ ክብር እና ነፃነት ከጣልቃ ገቦች ነፃ እንዲሆን አስፈላጊውን ጥበቃ ያደርጋል። ይህም የሆነበት ምክንያት "አንድ ደራሲ አንድን የድርሰት ሥራ ሲያወጣ ከኤኮኖሚ ጥቅሙ በላይ አንድ ልዩ የሆነ ሥራ ለዓለም ያስተዋውቃል። በዚህም ክፊል ስብእናውን በማስተዋወቅ ሥራዎቹ ለሕዝብ ጥቅም በመዋላቸው የተነሣ በደራሲው ላይ ከገንዘብ ጥቅሙ በላይ ሌሎች ጉዳቶች እንዲደርሱበት ሁኔታዎች ይፈጠራሉ።"[15] ስለዚህም ሕግ ለደራሲያን የሞራል መብቶች ዕውቅና መስጠቱ ደራሲያን እንዲህ ካሉ ጉዳቶች እንዲጠበቁ ለማድረግ ነው። በመሆኑም የሞራል መብቶች በመባል ከሚታወቁት መብቶች ዋና ዋናዎቹ አንድን ሥራ ለመፍጠር ያለመገደድ፣ ሥራው በደራሲው ሥም እንዲጠራ የማድረግ፣ ሥራው እንዳይለዋወጥ የማድረግ፣ ሥራውን በፈለገው መንገድ የማውጣትና የማሣተም፣ በሥራው ላይ የሚደረጉ ማናቸውንም የመቀነስ ወይም የማስተካከል ሥራ የመከልከል፣ የወጡ ሥራዎችን መልሶ የመሰብሰብና የማጥፋት እና የደራሲውን ስብእና ሊነኩ የሚችሉ ሌሎች ድርጊቶችን የመከልከል ናቸው።[16]

## 1·5· የተርጓሚዎች መብቶች

የትርጉም ሥራዎችን በተመለከተ ተርጓሚዎች በሕግ ከደራሲያን እኩል ይታያሉ። ይህም ማለት በሕግ ለደራሲያን የተሰጡ መብቶች ሁሉ ተርጓሚዎችም ይኖራቸዋል ማለት ነው። በዚህ ደረጃ ተርጓሚዎች የአዲስ ሥራ ፈጣሪዎች ናቸውን? ሕግ ተርጓሚዎችን ከደራሲያን እኩል አድርጎ የሚያያቸው ለምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ።

በመሠረቱ ትርጉም አንድን የድርሰት ሥራ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቀይሮ ማቅረብ ብቻ አይደለም። ትርጉም ከዚህ በላይ ችሎታን የሚጠይቅ የሥራ መስክ ነው። በመሆኑም ተርጓሚዎች የተለያየ ባሕል ያላቸውን ሕዝቦች የሚያገናኙ ድልድዮች እንደ መሆናቸው መጠን ከደራሲያን የበለጠ ኃላፊነትን የተሸከሙ ባለሙያዎች ናቸው። ይህም የተባለበት ምክንያት፡-

> አንድ የትርጉም ሥራ የደራሲውን ሥራ የሚቃረን መሆኑ ቀርቶ የወጥ ሥራ ደራሲውን ሀሣብ በሐቀኝነት የሚያስተላልፍ መሆን ስላለበት፣ ተርጓሚው የወጥ ሥራ ደራሲውን ሀሳብ በተቻለ መጠን ማወቅ እና እነዚህንም ለመግለጽ አስፈላጊውን ቃላት መጠቀም ስላለበት ነው። ከዚህም የተነሣ አንድ ተርጓሚ ወጥ ሥራው የተጻፈበትን እና የሚተረጉምበትን ቋንቋዎች እና የድርሰት ሥራው የተጻፈበትን ጉዳይ በሚገባ የሚያውቅና ትርጉሙም የራሱን ስብእና የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል። ከዚህም የተነሣ መተርጎም አዲስ ሥራን እንደ መፍጠር ይቆጠራል።[17]

እነዚህን ችሎታዎች የተጎናፀፈ ተርጓሚ ለአንባብያን እና ለወጥ ሥራው ደራሲ ታማኝ የሆነ መሆን ስለሚኖርበት የደራሲውን ሀሳብ በራሱ ሀሳብ መተካት አይኖርበትም። ስለዚህም የደራሲውን ሀሳብ ሊገባ በሚችልና ማራኪ በሆነ አቀራረብ ለአንባቢው ማስተላለፍ ይኖርበታል።

ከላይ በቀረቡት ምክንያቶች የተነሳ የትርጉም ሥራዎች እንደ ወጥ ሥራዎች ሁሉ ሕጋዊ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፤ ተርጓሚዎችም በሕግ ከደራሲያን እኩል ሆነው ይታያሉ።

---

15 ማርቲን ኤ ሮደር፣ ዘ ዶክትሪን ኦፍ ሞራል ራይትስ ኤ ስተዲ ኢን ዘ ሎው ኦፍ አርቲስትስ፣ ኦተርስ፣ ኤንድ ክሪኤተርስ፣ *ሃርቫርድ ሎው ሪቪው፣* ቅጽ 53 (1940) ገጽ 557

16 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 556። ይህ ጽሑፍ ከላይ ስለተጠቀሱት መብቶች በሰፋት ስለሚያብራራ አንባብያን ለበለጠ ማብራሪያ ጽሑፉን ቢያነቡ መልካምነው። የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ለደራሲያን የሞራል መብት በተለያዩ ቁጥሮች ሥር እውቅናን ይሰጣል። ቁ. 1671 የሕሊና መብት፣ 1673(3) የሕዝብ ባለሥልጣኖች መብት፣ 1665 የወጣውን ሥራ ስለመለዋወጥ 1674 የድርሰት ወይም የኪነጥበበት ባለሐብትነት (ጥበቃ) ይመልከቱ።

17 ጂ· ሬንጋ፣ *ሌ ድሩዋ ዴ፣ ትራዱክተር ሱር ል ፣ ፕላን ኢንተርናሲዮናል፣* ባቤል፣ ቅጽ 11፣ ቁ·2 (1956) ገጽ 73 እና የሚከተሉት በዚፕን ራይኮቪክ፣ ትራንስሌሽን ራይትስ ኤንድ ትራንስሌተርስ ራይትስ፣ *ኮፒ ራይት መንዝሊ ሪቪው ኦፍ ዘ ወርልድ ኢንቴሌክቹዋል ፕሮፐርቲ ኦርጋናይዜሽን ኤንድ ዘ ዩናይትድ ኢንተርናሽናል ቢሮ ፎር ዘ ፕሮቴክሽን ኦፍ ኢንቴሌክቹዋል ፕሮፐርቲ፣* 7ኛ ዓመት፣ (1971) በገጽ 195 እንደተጠቀሰው።

ስለዚህም ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የብዙ አገሮች ብሔራዊ ሕጎች ለተርጓሚዎች የሞራልና የኢኮኖሚ መብቶች እውቅናን ይሰጣሉ። ከዚህም በተጨማሪ የአንዳንድ ሀገሮች ሕጎች የትርጉም ሥራዎች ወጥና የፈጠራ ሥራን የሚያሳዩ መሆን አለባቸው[18] በማለት ሲደነግጉ የቀሩት ሀገሮች ሕጎች ግን የትርጉም ሥራዎች እንደ ወጥ ሥራዎች ሁሉ ሕጋዊ ጥበቃ ይደረግላቸዋል ከማለት በስተቀር ተጨማሪ መመዘኛ እንዲኖር አያስገድዱም።[19]

## 2· ትርጉምን የመፍቀድ መብት በዓለም አቀፍ ሕግ

የድርሰትና የኪነ ጥበብ ባለሐብትነት ዓለም አቀፋዊ ጥበቃ የሚያስፈልገው እና የዓለም አቀፍ ሕግ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ ነው። ከዚህም የተነሳ ትርጉምን የመፍቀድ መብት ዓለም አቀፋዊ ጠባይ ያለው መብት ነው። ስለዚህም ለአእምሮ ሥራ አፍላቂዎች አስፈላጊ ጥበቃ ለማድረግ ብዙ ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች ተፈርመዋል። ከነዚህ ስምምነቶች ውስጥ የሴፕቴምበር 9፣ 1886 የበርን የድርሰትና የኪነ ጥበብ ሥራዎች ጥበቃ ስምምነት (ከዚህ በኋላ የበርን ስምምነት ተብሎ የሚጠራው) እና የሴፕቴምበር 6፣ 1952 ዓለም አቀፍ የድርሰትና የኪነጥበብ ባለሐብትነት ስምምነት (ከዚህ በኋላ ዓለም አቀፍ ስምምነት ተብሎ የሚጠራው) በዋነኛነት ተቀባይነት ያገኙ ስምምነቶች ናቸው።[20]

የደራሲያን የራሳቸውን ሥራዎች የመተርጎምና ትርጉምን የመፍቀድ መብቶች በሁለቱም ስምምነቶች እውቅና የተሰጣቸውና ጥበቃም የሚደረግላቸው መብቶች ናቸው።[21] የበርን ስምምነት የጥበቃ ጊዜውን በአሥር ዓመት ሲገድበው የዓለም አቀፉ ስምምነት በሰባት ዓመት ይገድበዋል። የስምምነቶቹ ይዘት ይህን ቢመስልም ሁለቱም ስምምነቶች በዓለም ላይ አንድ ዓይነት አቋም እንዲኖር ለማድረግ ግን አልቻሉም። በድርሰትና ኪነጥበብ ባለሀብትነት ስምምነቶች ላይ በጣም አከራካሪ ሆኖ የሚገኘው ጭብጥ ለደራሲያን መብት ጠንካራ የሕግ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል የሚለው የበለጸጉ አገሮች ፍላጎትና የደራሲያን መብት የጥበቃ ጊዜ አጭር ሊሆን ይገባዋል የሚል አቋም ካላቸው በማደግ ላይ ካሉ አገሮችን ፍላጎት አኳያ ሚናዊነትን ማስፈን ነው።

የበርን ስምምነት በቅኝ ግዛት ዘመን በቅኝ ገዢዎች የተፈጠረ ሲሆን[22] በማደግ ላይ ያሉ አገሮች በቅኝ ገዢዎቻቸው ተወክለዋል ቢባልም በቀጥታ የተሳተፉበት ስምምነት አይደለም። ስምምነቱ በሥራ ላይ በዋለባቸው የመጀመሪያ ዓመታት አባል አገሮች ለዜጎቻቸው የሚሰጡት መብት ተመሳሳይ በመሆኑ እና የጋራ የሆነ መርሆዎችንም ስለተከተሉ ስምምነቱ ውጤታማ ነው ተብሎ ነበር።[23]

ሆኖም ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳበቃ እና ቅኝ አገዛዝ እየከሰመ ሲሄድ ከቅኝ ግዛት የተላቀቁ አገሮች "ዓለም አቀፋዊ የደራሲያን መብትን" በማስመልከት በተለያዩ መድረኮች ተቃውሞአቸውን በማሰማታቸው የበርን ስምምነት በጁን 1967 ዓ·ም

---

18 የጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ የ1965 ዓ·ም የድርሰትና ኪነ ጥበብ ባለሐብትነት ሕግ ቁ·3፣ የ1969 ዓ·ም የሐንጋሪ ሕግ ቁ·4(2)፣ የ1941 ዓ·ም የጣሊያን ሕግ ቁ·4፣ የ1961 ዓ·ም የፔሩ ሕግ ቁ· 8 እና የ1956 ዓ·ም የሩማንያ የድርሰትና የኪነ ጥበብ አዋጅ ቁ·10

19 የፍ·ሕ· በቁ· 1649(1) "የመጀመሪያው አዲስ ሥራ አውጪ መብት ሳይነካ የመጽሐፉ ትርጉም … እንደ መጀመሪያ ሥራ ሆኖ ይቆጠራል።" በማለት ይደነግጋል። በቁ· 1655 መሠረት ትርጓሚዎች እንደ ደራሲያን ሁሉ የትርጉም ሥራዎቻቸው በሌሎች እንደ ገና ሲተረጎሙ ድጋሚ ትርጉሙን የመከልከል ሥልጣን የላቸውም።

20 እዚህ ላይ የቀረበው ትንተና ሁለቱን ስምምነቶች ብቻ እንጂ ሌሎች ተመሳሳይ ስምምነቶችን አያካትትም። የሴፕቴምበር 9 1886 ዓ·ም· የበርን ስምምነት በሜይ 4፣ 1886 በፓሪስ አዲሽናል አክት ተሻሽሏል። በኖቬምበር 13 1908 በርሊን ላይ ተከልሷል። ማርች 20፣ 1914 በርን ላይ ተጨማሪ ፕሮቶኮል ታክሎበታል እንዲሁም ጁን 2 1928 ሮም ላይ፣ ጁን 26፣ 1948 ብራስልስ ላይ፣ ጁላይ 14፣ 1967 ስቶክሆልም ላይ እና ጁላይ 24 1971 ፓሪስ ላይ ተከልሷል። የዓለም አቀፉ ስምምነት ጁላይ 24፣ 1971 ፓሪስ ላይ ተከልሷል።

21 የሁለቱንም ስምምነቶች አንቀጽ 5 ይመልከቱ።

22 አላን ኤች ላዛር፣ ዴቬሎፒንግ ካንትሪስ ኤንድ አተርስ ራይትስ ኢን ኢንተርናሽናል ኮፒ ራይት፣ *ኮፒ ራይት ሲምፖዚየም*፣ ቁ· 19፣ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣ ኒው ዮርክ፣ ለንደን (1971) ገጽ 6

23 ዝኒ ከማሁ ገጽ 8 እና 9

ከላይ እንደተገለጸው የኢትዮጵያ የድርሰትና የኪነ ጥበብ ባለሐብትነት ሕግ ደራሲያን ለሥራዎቻቸው በሕግ የተሰጣቸው የጥበቃ ጊዜ እስከሚያልቅበት ድረስ ትርጉምን የመፍቀድ ብቸኛ መብት አላቸው ከሚለው ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነትን ካገኘው መሠረተ ሐሣብ የተለየ አቋም ወስዷል። ይህም በመሆኑ ሕጉ ይህን አቋም ሲወስድ የቻለው በምን ምክንያቶች የተነሳ ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ይህን በማስመልከት ሊነሱ ከሚችሉት ጥያቄዎች ጥቂቶቹ፡ ምንጩ በሆነው በፈረንሣይ ሕግ ተጽዕኖ ተድርጐበት ይሆን? የኢትዮጵያ ባሕል ወይም የባሕል ሕግ ተጽዕኖ አድርጐበት ይሆን? ሕጉ በመዘጋጀት ላይ በነበረበት ወቅት ይህ ነጥብ ተነስቶ ውይይት ተደርጐበት ይሆን? ውይይት ከተደረገበትስ በምን መልኩ ተወሰነ? የሚሉት ናቸው። በሚቀጥሉት ፓራግራፎች ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ተሞክሯል።

ከላይ እንደተገለጸው የማርች 11 ቀን 1957 ዓ.ም. የፈረንሣይ የድርሰትና የኪነ ጥበብ ባለሐብትነት ሕግ እንዳለ ተወስዶ በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ ገብቷል።[50]

በመሆኑም የኢትዮጵያ የድርሰትና የኪነጥበብ ባለሀብትነት ሕግ ብቸኛ ምንጭ ይህ የፈረንሣይ ሕግ ነው ማለት ይቻላል። የዚህ የኛ ሕግ ምንጭ የሆነው የፈረንሣይ ሕግ አንቀጽ 40 ግን ደራሲያን ድርሰቶቻቸው ሲተረጎሙ የመፍቀድ ወይም የመከልከል መብት እንዳላቸው በግልጽ ይደነግጋል። ከዚህም በተጨማሪ ፈረንሣይ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አባል ስትሆን ከእንግሊዝ ጋር የፓሪስ ስምምነት በመባል የሚታወቀውን እና የደራሲያንን ትርጉም የመፍቀድ መብትን የሚቀበለውን ስምምነት በኖቬምበር 3 ቀን 1851 ዓ.ም የፈረሙች አገር ናት።[51] ስለዚህም የኢትዮጵያ ሕግ ትርጉምን የመፍቀድ መብትን በማስመልከት ለወሰደው የተለየ አቋም ምንጩ (ምክንያቱ) የፈረንሣይ ሕግ አይደለም ማለት ይቻላል።

በኢትዮጵያ የድርሰትና የኪነ ጥበብ ባለሐብትነት ሕግ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያለው በ1952 ዓ.ም (እ.ኢ.አ.) የፍትሐ ብሔር ሕጉ ሲታወጅ መሆኑ ከላይ ተመልክቷል።[52] ስለዚህም የፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 11 እንደ ሌሎቹ የሕግ ክፍሎች ሁሉ በኢትዮጵያ ባሕል ወይም የባሕል ሕግ ተጽዕኖ ተደርጎበታል ማለት አይቻልም። በተጨማሪም በአገሪቱ ባሕልም ሆነ የባሕል ሕግ በደራሲያን መብት ላይ እንዲህ ያለ ገደብ መኖሩን የሚያመለክት ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም።

የኢትዮጵያ የድርሰትና የኪነ ጥበብ ባለሐብትነት ሕግ በአርቃቂው ኮሚሽን ውይይት ሲደረግበት በሚከተለው ሂደት ውስጥ አልፏል። አርቃቂው ሬኔ ዴቪድ አንድ ምዕራፍ የያዘ "ሻፒትር II ድ.ላ. ፕሮፕሬዮቴ ሊትሬር ኡ አርቲስቲክ" የሚል ረቂቅ በፈረንሣይኛ አዘጋጅተው ለኮሚሽኑ አቀረቡ። በመጨረሻም የፈረንሣይኛው ረቂቅ ቁ. 36–63 የነበሩት ከመጠነኛ ለውጥ ጋር የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁ. 1647–1674 ሆነው ተቀረጹ። ለኮሚሽኑ በቀረበው የፈረንሣይኛ ረቂቅ ቁ. 44 መሠረት ደራሲያን የድርሰቶቻቸውን ትርጉም መከልከል አይችሉም።[53] ስለዚህም ይህ የፈረንሣይኛው ረቂቅ ቁ.44 ሕጉ ሲታወጅ ያለ ምንም ማሻሻያና ለውጥ የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ. 1655 ሆኖ ወጥቷል።[54]

---

50 ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 39 የተጠቀሰውን ይመለከቷል።

51 ፌንከልስቴይን ኤች ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 27 የተጠቀሰውን ገጽ 53 እንዲሁም የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 6 ይመለከቷል።

52 ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 38 የተጠቀሰውን ይመለከቷል።

53 የፈረንሣይኛው ቅጂ እንደሚከተለው ይነበባል። Traductions
(1) - L' auteur ne peut s' opposer a la traduction de son oeuvre
(2) - La traduction faite sans 1' autorasation de 1' auteur doit mentionner defacon express, au debut de 1' overage cette circonstance.
(3) - Faute de cette mention, elle est reputee porter atteint aux droit de 1' auteur."

54 *ሲቪል ኮዲፊኬሽን ማቴሪያልስ* ቡክ 3 ፕሮፐርቲ (ያልታተመ፣ ሕግ መጽሐፍት ቤት) ገጽ 12–20 እና 177ን እንዲሁም ለተደረጉት ማሻሻያዎች የጃንዋሪ 8 1958 ቃለ ጉባዔን ይመልከቱ።

የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁ· 1655 አሁን ባለበት መልኩ እንዲቀረጽ ያስቻለው የሕግ አውጭው ፍላጎት ምን እንደ ነበር የሚያረጋግጡ አሳማኝ ሠነዶች በማይገኙበት ሁኔታ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ከግምት የራቀ አይደለም። ቢሆንም በመልስነት ሊቀርቡ ከሚችሉ ምክንያቶች አንዱ የሕግ አውጭው ፍላጎት አገሪቷ በበለጸጉት አገሮች ከሚወጡ የድርሰት ሥራዎች በተለይም ለትምህርት ጉዳዮች በቀላሉ እንድትጠቀም ለማስቻል ነው የሚል ሊሆን ይችላል። ይህ ምክንያት ከላይ እንደ ተገለጸው በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ ድርድር በሚደረግበት ወቅት ብዙ ታዳጊ አገሮች የያዙት አቋም ነው። ይህ አሳማኝ ምክንያት ቢመስልም ኢትዮጵያ እስከ አሁን ድረስ የየትኛውም የዓለም አቀፍ የድርሰትና የኪነ ጥበብ ባለሐብትነት ስምምነት አባል ስላልሆነች ከሀገር ውጭ ለሚወጡ የድርሰት ሥራዎች ሕጋዊ ጥበቃ የማድረግ ግዴታ የለባትም። ስለዚህም የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ተፈፃሚነቱ በሀገር ውስጥ ለሚሠሩ ሥራዎች እንጂ ከአገር ውጭ ለሚሠሩ ሥራዎች አይደለም። ይህም ሆኖ ሕጉ በሚረቀቅበት ጊዜ ማለትም እ·ኤ·አ· በ1958 ዓ·ም የሕግ አርቃቂ ኮሚሽኑ የድርሰት ሥራዎች ለትምህርት ጉዳይ የሚውሉበትን መንገድ ፍጹም አልተገነዘበም ማለት አይቻልም። ምክንያቱም በወቅቱ የረቂቁ ቁ· 49 የአሁኑ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ· 1660 የሚከተለውን ንዑስ ቁጥር እንዲይዝ ተደርጎ ቀርቦ ነበርና ነው።

(3) የድርሰት ሥራዎች መታተም ካበቁ በኋላ ለትምህርት ጉዳይ ሲባል ሥራዎቹ እንዲባዙ መፍቀድ ይቻላል።[58]

ሆኖም ባልታወቀ ምክንያት የበላይነት ያለው የሕጉ የአማርኛ ቅጂም ሆነ የእንግሊዝኛ ቅጂው ይህንን ንዑስ ቁጥር ሳይጨምሩ ወጥተዋል። ከዚህም በተጨማሪ የሕዝብ ባለሥልጣኖች ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የድርሰት ሥራዎች እንዲታዩ፣ እንዲባዙ ወይም እንዲሰሙ የመፍቀድ ሕጋዊ ሥልጣን ስለተሰጣቸው ይህ ሥል ጣን ለትምህርት ጉዳይ በሚዉሉ የድርሰት ሥራዎች ላይ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት ሊኖር ይችላል።[59] ይህም ሆኖ የሕግ አውጭው ፍላጎት ትምህርትን ከማስፋፋት አንፃር በደራሲያን መብቶች ላይ ገደብ ሊደረግበት ይገባል የሚል ነበር ቢባል እንኳ የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁ· 1660 ወይም 1673 ትርጉምን የመፍቀድ መብትን አያካትቱም። ምክንያቱም በቁ· 1655 መሠረት መተርጎም ለሁሉም በነፃ የተሰጠ መብት በመሆኑ ነው። ስለዚህም ትርጉም መፍቀድን በተመለከተ በደራሲያን መብቶች ላይ ገደብ እንዲኖር ያስፈለገበት ምክንያት ለትምህርት ጉዳይ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ አይቻልም። ይህ ቢሆን ኖሮ ሕግ አውጪው መብቱን ለደራሲያን ሰጥቶ ለትምህርት ጉዳይ ከሆነ በቁ· 1660 ወይም 1673 ሊገድበው ይችል ነበር።

የሕግ አውጭው ፍላጎት ምን እንደነበር ግልጽ ባልሆነበት ሁኔታ ሌላም ምክንያትም ሊኖር ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል። ይኸውም የሕግ አውጪው ፍላጎት ተርጓሚዎች የትርጉም ፍቃድ ማግኘት ወይም ከማንም ፍቃድ መጠየቅ ሳያስፈልጋቸው የድርሰት ሥራዎችን በመተርጎም እና ሥራዎቻቸውንም ለሕዝብ በማድረስ የአገሪቱን የሥነ ጽሑፍ ባሕልን ለማሳደግ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ የሚል ነበር ማለት ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ ዓላማው በአገሪቱ ውስጥ ባሉት የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪ ሕዝቦች መካከል የባሕል ቅርርብና ውህደትን መፍጠር ነበር ማለትም ይቻላል። ይህ ዓላማ የተቀደሰ ዓላማ ነው ማለት ቢቻልም የኢትዮጵያ ተርጓሚዎች ይህንን ሕጋዊ ነፃነት በታሰበለት ዓላማ መሠረት ተጠቅመውበታል ወይ? የሚለው አከራካሪ ነጥብ ሊሆን ይችላል። ይህም ሆኖ በአገሪቱ ውስጥ ባሉ መጽሐፍት መሸጫ መደብሮች መደርደሪያዎች ላይ ያሉትን መጽሐፍት በማየት በግልጽ ለማወቅ እንደሚቻለው የአገሪቱ ተርጓሚዎች ከአንድ ወይም ከብዙ ምክንያቶች የተነሳ በአገሪቱ ውስጥ ባሉ ቋንቋዎች የተጻፉ መጽሐፍትን ወደ ሌላ የአገር ውስጥ ቋንቋ የመተርጎም ፍላጎት እስካሁን አላደረባቸውም የሚል

---

58 ሲቪል ኮዲፊኬሽን ማቴሪያልስ ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ· 53 የተጠቀሰውን የረቂቁን ቁ· 79 ይመልከቱ። የፈረንሣይኛው ቅጂ እንደሚከተለው ይነበባል።
Les Copies ou reproductions sont authorisees plusieurs exemplaires, a des fins d' ensignement, lorsque 1' ouvre est epuise.

59 የፍ·ሕ·ቁ·1673

